# የዳሽን ቢራ ፋብሪካ ውዝግብ እስካሁን መፍትሔ እንዳልተገኘለት ተገለጠ

በሰሜን ጎንደር በጎንደር ከተማ አባ ሣሙኤል በተባለ ሠፈር ባለው በዳሽን ቢራ ፋብሪካ አስተዳደርና በሠራተኛው ማህበር አመራር አባላት መካከል የተፈጠረው ውዝግብ እስካሁን መፍትሔ እንዳልተገኘለት የውስጥ ዐዋቂ ምንጮች ሰሞኑን ገለጡ።

እንደ ምንጮቹ አገላለፅ ውዝግቡ ሊፈጠር የቻለው የፋብሪካው ሥራአስኪያጅ በሠራተኛው አመራር ላይ ሌላ የአመራር አካል በመፍጠራቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

ይህንኑ ውዝግብ በውይይት ለመፍታት በአቶ በረከት ስምኦን በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪ የተመራ አቶ ዮሴፍ ረታና አቶ የወንድወሰን የሚገኙበት የፋብሪካው ቦርድ ሰሞኑን ወደ ጎንደር ሄዶ የተመለሰ ሲሆን እነዚህ የቦርድ አባላት አቶ ብርሃኑ አድማሱ የተባሉትን የፋብሪካውን ሥራ አስኪያጅ ከማነጋገር በስተቀር ውዝግቡን ለመፍታት አንዳችም ተጨባጭ እርምጃ እንዳልወሰዱ ምንጮች አስታውቀዋል።

ባሁኑ ወቅት 1. ደጀኔ ታረቀኝ የቀድሞ የሠራተኛው ማህበር ሊቀመንበር 2. ዳንኤል ዓለማየሁ ም/ሊቀመንበር፤ 3. ነጋ ካሴ ፀሐፊ እንዲሁም ሌሎች ሃያ የሚሆኑ የፋብሪካው ሠራተኞች ከሥራ ተባርረው የፋብሪካውን አስተዳደር በመክሰስ ላይ እንደሚገኙም ለማወቅ ተችሏል።

EthioLion.com

# የደጀን ከተማ ነዋሪዎች ድብደባ እንደ ተፈፀመባቸው ተሰማ

በምሥራቅ ጎጃም ዞን በደጀን ወረዳ የደጀን ከተማ ነዋሪዎች እንዲሁም በሥራ ምክንያት በከተማው ውስጥ የተገኙ ባለጉዳዮች ሁሉ በፖሊሶችና በአካባቢው ታጣቂዎች ነሐሴ 15 ቀን 2000 ዓ.ም ከፍተኛ ድብደባ እንደተፈፀመባቸው ተሰማ።

በዕለቱ ታጣቂዎቹ የተመደበላቸውን ቦታ በስምሪት ይዘው ከቆዮ በኋላ ከምሽቱ 2 ሰዓት ተኩል ሲሆን የከተማውን መብራት በማጥፋት በከተማ ውስጥ ለግል ጉዳይ በመንቀሳቀስ ላይ የነበረውን ሰላማዊ ሰው ሁሉ በዱላ መቀጥቀጥ እንደ ጀመሩ የዓይን ምሥክሮች አረጋግጠዋል።

በዚህ ወቅት በዋናነት ድበደባውን የፈፀሙት 1. ወታደር ሙሉቀን ደያስ 2. ወታደር ዓለም 3. ወታደር ከበደ 4. ታጣቂ እንዳለው ተረፈ 5. ታጣቂ ድረስ በፈቃዱና ሌሎች ሶስት ታጣቂዎች እንደነበሩ ታውቋል።

እንደ መረጃ ምንጮች አገላለፅ የጅምላ ድብደባው የተጀመረው በደጀን ከተማ ውስጥ የሚገኙ ድንጋይ ጫኞች፣ ተሸካሚዎች፣ የቀን ሠራተኞች፣ ጫማ ጠራጊዎችና ጎዳና ተዳዳሪዎች የብሔረ አማራ ደሞክራሲያዊ ንቅናቄ /የብአደን/ አባል እንዲሆኑ ተጠይቀው ፈቃደኛ ሳይሆኑ በመቅረታቸው እንደሆነ ታውቋል።

ቀደም ሲል በእነዚህ የሙያ መስኮች የተሰማሩ የከተማ ነዋሪዎችን ብድር እንደሚሰጣቸው ተናግረው የአገዛዙ አካላት አደራጅተቸው እንደነበርም ምንጮች አስታውቀዋል።

በዕለቱ በተፈፀመው ከፍተኛ ድብደባ ጉዳት ከደረሰባቸው መካከል 1. ጌትሽ ክብረት 2. መሐመድ ጌትነት 3. አልዩ ይማምና 4. አዲሱ ታመነ የተባሉ ወጣቶች ይገኙባቸዋል።

Ethiolion.com